## *አዲሱ የሐዋርያ እትም ከብዙ ጥንቅሮቹ ውስጥ ይሚከተሉትን አካቷል፦*

1) **ቆይታ ከክቡር ኢንጅነር ሃይሉ ሻወል፥ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ፕረዚደንት ጋር**

***"…ብዙ ጊዜ ስህተት እድርገናል፡፡ አለም አቀፍ ድርጅቶች እኛን ይደግፋሉ፥ ለዴሞክራሲ ቆመዋል የሚባል ብዙውሬ አለ፡፡ይሄን በአሁኑ  የትግል ሂደት ትክክል እንዳልሆነ ተረድተናል፡፡ ስለዚህ እኛ በራሳችን ሰዎች፥ በኢትዮጵያና ውጭ ባሉ ወገኖች መመካት እንጅ ሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች መጥተው ይረዱናል ብሎ መገምነቱ ከንቱ ነው፡፡" ኢንጅ. ሃይሉ ሻዎል***

*2)* **"ሕዝብ የመብትና የነጻነት ጥያቄዎችን አንስቶ በትግሉ ፍኖት በሚጓዝበት ወቅት፥ የፖለቲካውን መዘወር ጨብጠው ተሳፋሪውን ሕዝብ ህልፈታችን ከአንተ በፊት ትሆናለች የሚሉ አስመሳይ ደንገጡሮች በየደረጃው ክፉ ሽል ሆነው ተወልደዋል፡፡ እነዚህ አሳዊ ፖለቲከኞች ላጡ ለነጡ የፖለቲካ ነድያን "ሥልጣን የሕዝብ ነው!" የሚለውን መፈክር ቢያነሱም፥ ባነገቡት መፈክር አፎት ውስጥ የታጠቁት ስለት ለሥልጣን ይበቁ ዘንድ የሕዝቡን ክርና ማግ - አንድነቱንና ግንኙነቱን- መቁረጫ መበጠሻቸው በመሆኑ፥ መሠረታዊው ሕዝባዊ መፈክር የአባባላቸው አቃቂር ከመሆን አላለፈም፡፡ የሕዝብን የበላይነት እውን ለማድረግና የሀገርን ሉአላዊነት ለመጠበቅ ሲሉ እጅግ ብዙ ሰማእታት ታግለው በወደቁበት የትግል ጥርጊያ ላይ፥ የገቡትን ቃል ኪዳን ረስተው ተክለ-ሰውነቶቻቸውን የሚያሰማምሩ ግብዞች ብቅ እያሉ ከፍተኛ ጉዳት በየጊዜው አድርሰዋል፡፡ እነኝህን መሰል ቡክኖች መጨረሻቸው አይወድቁ ውድቅት፥ አይከስሩ የታሪክ ክስረት መሆኑን ግን፥ ነገ ከነገ ወዲያ በሕዝብ ትግል ክሳራ "አጅሬ" ለመባል ልባቸው የሚሻቅል ሁሉ ትምህርት ቢወስዱበት ምንኛ በተገባ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ትምህርቱ አጥጋቢ አይደለ ይመስል በየጊዜው ከመከሰቱ በላይ፥ በዚህ አይነቱ የታሪክ ሞት የሚሰናበቱት የሥልጣን ሰፍሳፎች ብቻ ሳይሆኑ እየቀደሙ ተፍ ተፍ በማለታቸው፥ የመሯቸውና ያታገሏቸው እየመሰላቸው እስከመጨረሻቸው አብረዋቸው የቆሙት አንዳንድ የየድርጅቶቻቸው አባላትና ጨዋ የሕዝብ ወገኖች ጭምር ናቸው በዚህ አይነቱ  የታሪክ ማቅ ተሸብልለው አብረው የሚቀበሩት፡፡" …ከሐዋርያ ርእሰ አንቀጽ  የተቀነጨፈ**

## 3) **ከደብዳቤዎች …**

### **ቁርጡን ንገሩን፤**

**ሰላም የሐዋርያ አዘጋጆች፥ እንደምን ከረማችሁ፥ እንደምን ባጀችሁ!! ስለቅንጅት አዝነን ሳንጨርስ ኢሕአፓ ዉስጥ ተፈጠረ በተባለው ችግር ግራ ተጋብተናል፤ እውነቱን ቁልጭ አድርጎ የሚነግረን በመጥፋቱ ቦታ ቦታችን ለመያዝ ተቸግረናልና  እባካችሁ አንድ በሉን፡፡ ሐዋርያም እንደተለመደው ወቅቷን ጠብቃ ባለመውጣቷ አቋሟን ማወቅ አልቻልነም፤ መቸም አሁን ሳትወድ በግዷ መውጣቷ አይቀርም በሚል ይቺን የጭንቀት ደብዳቤ ልኬላችሁዋለሁና አንድ በሉን፤ የሐዋርያ አቋም ምንድን ነው?**

**የጨነቀው ከቶሮንቶ**
……… …….

## ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም

*ይድረስ ለሐዋርያ አዘጋጆች፥*

*እንደ ቅንጅት ባሉ የሕዝብ ድጋፍ ባላቸው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ደርሶ ያየነው አሳዛኝ ሁኔታ በኢሕአፓ ውስጥም ተከሰተ መባሉ በጣም አስደንጋጭ ነው። ኢሕአፓ የሚታወቀው በፖለቲካ ልምዱና በአባላቱ ብስለት መሆኑን ማንም ኢትዮጵያዊ አይክደውም። እርስ በርስ ተፋልሶ የገዛ ድርጅት ማፍረስን የኢሕአፓ አባላት በጅልነት ፈርጀው እጅግ የሚስቁበትና የሚኮንኑት አድርጌ ነበር የምመለከተው። ጉድ ሳይሰማ መከረም አይጠባም እንደሚባለው ኢሕአፓንም የዘመኑ የፖለቲካ በሽታ አጠቃው የሚባለውን ዜና ስሰማ እኔ በበኩሌ እየቀለዱ መሆን አለበት ነው ያልኩት፤ ማመን በፍጹም አልቻልኩም፤ አሁንም ቢሆን ገና አላመንኩም። ለማንኛውም ሐዋርያ የሕዝብ ጋዜጣ ናትና ሐቁን ፍርጥርጥ አድርጋ ማሳወቅ ይጠበቅባታ። ሳትዘገዩ አሳዉቁንና እርማችን እናውጣ ወይም እንጽናና።*

*መልስ የምሻ ታዛቢ*
*ከመካከለኛው ምስራቅ*

***<u>ሐዋርያ፡-</u>*** *ክቡራትና ክቡራን ወገኖች፥ ከሁሉም በማስቀደም የሕዝብና የሀገር ጉዳይ ከንክኗችሁ ክፉውን ጠልታችሁ፥ በጎውን ተመኝታችሁ እውነቱን ለማወቅ በመጣራችሁ ጥልቅ ምስጋናችን ይድረሳችሁ። ከላይ የቀረቡልንን የመሳሰሉ በዛ ያሉ ደብዳቤዎችና የስልክ ጥሪዎች ሲደርሱን ሰንብተዋል። እንደሁላችሁም ነገሩን በጥሞና፥ ነገር ግን ዘለቅ ጠለቅ ብለን ተከታትለነዋል። ሕዝብ የመጠየቅና የማወቅ መብት ስላለው በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽነት አስፈላጊ ነው።*

*ሐዋርያ ነጻ ጋዜጣ ናት። ይህ ሲባልም የራሷ የሆነ ቅኝት የላትም ማለት ሳይሆን፥ ወይም ደግሞ ወገንተኝንነቷ የሚገለጽበት ጎራ የለም ማለት ሳይሆን፥ ነጻነቷ በማንም ቁጥጥር ሥር ያልወደቀች ሆና ከተለያዩ አቅርቦቶች በተጨማሪ ህብረተሰባችንና ሀገርን በተመለከተ የሚንሸራሸሩ ገንቢ ጉዳዮች ያለገደብ አቅም በቻለ መጠን ይስተናገዱባታል ማለት ነው።*

*ሐዋርያ ወገንተኝነቷ ሕዝባዊነቷ ነው። ሕዝብንና ሀገርን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ምንጊዜም የሕዝብን የበላይነት ተቀብላ ለቷሚላ መብቶቹና ነጻነቱ የሚያደርገውን ትግል ትደግፋለች። በየምክንያቱ ከሕዝብ የትግል ጎራ ራሳቸው ያወጡትን ህግ እየጣሱ የሚስፈነጠሩትን አትከተልም፤ ለትልቁ ጥያቄ - ለሕዝብ መብትና የነጻነት ትግል- ቅድሚያ ሰጥታ ህግና ደምብ ተከትለው አብዛኞች ወስነው የሚያካሂዱትን ትግል በጥብቅ ታበረታታለች፥ ትወግናለች። ኢሕአፓ ውስጥም ሆነ በቅንጀት መካከል የተሰማውና የታየው ችግር እንደ ሐዋርያ ያሉ ዜና ደዋሪ ተቋሞችን ብቻ ሳይሆን ከዳር እስከ ዳር - ከባላንጣ እስከ ወዳጅ ያለውን ሕዝብ - ለአንዳፍታ ፍዝዝ ያደረገ ነዛሪ ዜና ነበር። እውነቱ መነገር አለበት - ትግሉ ይቀጥላል። ኢሕአፓ አስቸኳይ አጠቃላይ የአባላት ተወካዮች ጉባኤ አካሂዶ ድርጅቱ ሲከተለው በቆየው ህገ-ደንቡ መሠረት በጉዳዮቹ ላይ ተነጋግሮ፥ አዲስ የአመራር አባላቱን በመምረጥ የትግሉን ቃልኪዳን አድሶ መቀጠሉን አረጋግጧል። በአባላቱ ስብሰባ ሂደት ላይ ህጋዊውን ጉባኤ ረግጠው የወጡት አነስተኛ ሉዑካኖች፥ በቁጥራቸው የመነመኑ ከመሆናቸው በላይ፥ አንኳር የሆነውን የዴሞክራሲ ህግ የተጋፉ ናቸውና ተቀባይነት የሚኖራቸው አይመስለንም፤ ሐዋርያን በተመለከተ ግን የነሱን ፈለግ ከቶም አትከተልም፤ በቅንጅት ያለውም ይኸው ነው።*

4) *“ሽብርተኛው የመለስ ቡድን በሰው ሀገር ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ ከመበጥበጡ በተያያዘ ደግሞ ሀገራችንን ከመቸውም በበለጠ እያተራመሰና እያቆሰለ መሆኑ የሚታይ ነው። ሀገሪቷን ለመሸጥ ሁሌም ዝግጁ ነውና ሱዳንን ለማስደሰትና ከጎኑ ለማቆየት ሲል የኢትዮጵያን መሬት አሳልፎ ሰጥቷል። ከቋራ ድንበር አንስቶ እስከ ኦሜድላና አሶሳ አዋሳኝ ሱዳን ይገባኛል ያለው ሁሉ ሊለቀቅለት ስምምነት ተደርሷል። በአንፃሩ ሱዳን በታያና ባሶንዳ ወዘተ ከኢትዮጵያ ወሰደ የተባለውን መሬት ጠያቂ አላገኘም።” ..መስፍን ታምራት በዜናው ባሻገር አምዱ ከሚያቀርበው*

5) *“የሥዕል ጥበቦች ተሰጥኦዎች ሕዝብና አገር ክብራቸውና ልእልናቸው ጥያቄ ላይ ሲወድቅ እውነትን በቆራጥነት ካልገለጡ ዘላቂ እሴት አይኖራቸውም፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ፈተና ላይ በወደቁበት ዘመን አገራዊ ክብራችንን፥ ግለሰባዊ መብታችንን በእኩልነት፥ በህጋዊነትና ዴሞክራሲያዊ አግባብ እንደገና እያነሱ ተከባብረንና ተፋቅረን እንደዜጋ እንድንኖር ለሚያጽናኑን፥ ከእንቅልፋችን ለሚቀሰቅሱንና መንፈሳችንን ለሚያድሱ እንደ አያሌው መስፍን ላሉየኪነ ጥበብ ሰዎች ልዩ አክብሮት አለኝ፡፡” .... ሻለቃ ግርማ ይልማ ' ቅሌትና እውነት' በሚል ርእስ ከሚያቀርቡት ሰፊ መጣጥፍ የተወሰደ፤*

6) **“ባለፈው ጽሁፌ ውስጥ አስታውሳችሁልኝ ከሆነ ምስጢረ ሜታፊዚክስ አላወራረድኩም፡፡ እሱ ግን፥ ቀሪ ዘመናችንን ሙሉ ስንነታረክና ስንናጭ የምንኖርበት ርእስ ነው፡፡ ይዘቱ ራሱ ወለፈንዲ የሆነ መያዣና መርጨበጫ ይሌለው ሙልጭልጭ ኩነት ነው፡፡ በግዙፉ ዓለማችን ውስጥ ከሚጨበጡትና ከሚዳሰሱት ግዙፋን ኩነቶች ባሻገር የሚታየውና የሚሰማው ነገር ረቂቅ ኩለንታዊ ባህርዩን ለመረዳት ዘመናት የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡ በግልጽ ለመናገር፥ ቢያንስ በእኔ እድሜ የጭብጣዊ ምንነቱ ጫፍ የሚደረስበት አይመስለኝም፡፡ እስከዚያው ግን ንትርኩ በየጊዜው እየጦዘ ይቀጥላል፡፡**

**ይሄን ነጥብ እዚህ ያነሳሁት “እብዮት” ተካሂዶበታል በምትባለዋ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደገና የሃይማኖት ነገር ማንሳት “ነውር” እና “ሃራም” ነው የሚሉ ወገኖች እንደማይጠፉ በማመን ነው፡፡ የብዙ ጊዜ ችግራችን ሆኖ የ ረው ነገሮችን ከሕዝባችንና ከሀገራችን መሠረታዊ ጭብጥ ጋር አዛምደን ያለውን ግዙፍ “ሪአሊቲ” ሳናገናዝብ የሆይ ሆይ ሠንጋ ፈረስ ላይ ተቀምጠን መሸምጠጣችን ነው፡፡ “ይልሂቃኑ” በሉት “የምጡቃኑ” አሌያም “የሥሉጣኑ” ማህበረሰብ ክፍል ቆንጣጭ ችግሩ ሆኖ ኖሯል፡፡ የቀመር ሰንጠረዥ (ስታቲስቲክስ) ማንጎድጎድ አያስፈልግም እንጅ ከሕዝባችን ውስጥ ከመቶ ስንቱ እጅ ነው በሃይማኖት ወይም “በማርያም እመ አምላክነት” የሚያምነው ብሎ መጠየቅም ሆነ ማሳየት በተቻለ ነበር፡፡ ”** *...ገሞራው (ሃይሉ) ከሚያቀርበው ሰፊ ሃተታ የተቀነጨበ*

7) **ሌሎችም ምንባቦች ተሟልተው ቀርበዋል፡፡ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ በሐዋርያ ድህረ ገጽ ላይ (www.hawarya.net) እልፈን አልፈን ስለምናቀርብ ተከታተሉ፡፡**

***ሐዋርያን በአዲስ መንፈስና ጥንካሬ ስርጭቷን ቀጥላለች፤ ጋዜጣዋን ማዘዝ ወይም ጽሁፍ ማቅረብ የምትሹ ሁሉ በአድራሻችን፡-***


Hawarya
1116 Wilson Ave.
Toronto, Canada
M3M 1G7

OR
email: hawarya.publications@sympatico.ca

Tel: 416-459-5964


***ልታገኙን ትችላላችሁ፡፡***